በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን
የሰሜን ካልፎርንያ ነቫዳ አሪዞና  ሀገረ ስብከት
ጽ/ቤት

THE ETHIOPIAN ORTHODOX TEWAHEDO CHURCH
ARCHDIOCESE OF NORTHERN CALIFORNIA, NEVADA,
ARIZONA MAIN OFFICE

"For God so loved the world, that he gave his only begotten Son, that whosoever believeth in him should not perish, but have everlasting life." John 3:16

ቀን፡07/09/2018 ዓ.ም
Date: 05/14/2026
ቁጥር: ሰካነአሀጽ/2014/18
Ref. No.2014/2026

**በሰሜን ካሊፎርኒያ ኔቫዳ እና አሪዞና ሀገረ ስብከት ለምትገኙ  የኢት/ኦ/ተ/ቤ/ክርስቲያን አድባራት እና ገዳማት እንዲሁም ለሚመለከተው ሁሉ ፤**

**ጉዳዩ፤ ከኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን መዋቅራዊ አሠራር ውጭ የተፈጸመውን ሕገ ወጥ እና ኢ-ቀኖናዊ ድርጊት ማውገዝን  እና መደረግ  የሚገባውን ጥንቃቄ  ማሳወቅን ይመለከታል፤**

በቅርብ ጊዜ የኢት/ኦ/ተ/ቤ/ክርስቲያን በሰሜን ካሊፎርኒያ ኔቫዳ እና አሪዞና ሀገረ ስብከት  በሳክራሜንቶ ከተማ በካልፎርንያ እስቴት በሕግ የመዝገብ ስማቸው Yohannes Tesfamariam Alemu ወይም አባ ዮሃንስ የተባሉ ግለሰብእ ከኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን መዋቅራዊ አሠራር ውጭ  በሀገረ ስብከቱ ፈቃድ እና እውቅና  ሳይሰጠው ***"ኢድያመ ዮርዳኖስ ዳግማዊ ወንቅሸት ቅዱስ ገብርኤል ወቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን"*** በሚል ስያሜና ቤተ ክርስቲያን በሚመስል ሕገ ወጥ የሃይማኖት ድርጅት ፈቃድ ምዝገባ በማድረግ እና የቦታ ግዢ በመፈጸም ኢ-ቀኖናዊ ድርጊት መፈጸማቸው እንደተሰማ ሀገረ ስብከቱ በቅርብ ጉዳዩን  በመከታተልና በተጨባጭ  መረጃዎችን በማሰባሰብ የተፈጸመውን ሕገ ወጥ ድርጊት ለማረጋገጥ ችሏል። እንዲሁም በሕገ ወጥ መንገድ የፈጸሙቱን ኢ-ቀኖናዊ ድርጊት  አውግዟል።

ስለሆነም ከላይ የተጠቀሱት ግለሰብእ በሀገረ ስብከታችን እንዲህ ያለውን ኢ-ቀኖናዊ ድርጊት መፈጸማቸው ከተረጋገጠበት ጊዜ አንስቶ ሀገረ ስብከቱ ከሚመለከታቸው የሕግ አካላት እና በሰሜን ካሊፎርንያ ወረዳ ቤተ ክህነት ሥር ከሚገኙ  የአጥቢያ  አብያተ ክርስቲያናት አስተዳዳሪዎች፤ አገልጋይ ካህናትና ዲያቆናት ጋር ሰፊ ውይይት በማድረግና የተፈጸመውን ሕገ ወጥ ሥራ በማውገዝ ሁሉም የሚመለከታቸው አካላት ሕገ ቤተ ክርስቲያንን ለማስከበር አስፈላጊውን ትብብር እንዲያደርጉና እንዲያወግዙ መመሪያ በመስጠት ወደፊት ሊደረግ የሚገባውን ሕጋዊ አሠራር  ከሕግ ባለሙያዎች ጋር በመመካከር አስፈላጊውን ቅድመ ሁኔታ በማመቻቸት ላይ ይገኛል።

ስለዚህ በሀገረ ስብከታችን እና በመላው የሰሜን አሜሪካ አህጉረ ስብከት በአጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት የምትገኙ አገልጋይ ካህናት፤ ዲያቆናት ፣ የሰንበት ትምሕርት ቤቶች መዘምራንና መዘምራት እንዲሁም  ምእመናንና ምእመናት በሙሉ ከላይ የተጠቀሱት ግለሰብ እ በማንአለብኝነት ከሚፈጽሙት ሕገ ወጥ እና ኢ-ቀኖናዊ ድርጊት ራሳችሁን  በመጠብቅና ድርጊቱንም በማውገዝ አስፈላጊውን ትብብር እንድታደርጉና የቅድስት ቤተ ክርስቲያን ክብር፤አንድነትና መዋቅራዊ አስተዳድር እንድታስከብሩ በእግዚአብሒር ስም እናሳስባለን።

እንዲሁም መላው የማህበራዊ ሚዲያ አካላት እና የሚዲያ ተቋማትም በእኒህ አምባ ገነንና የቅድስት ቤተ ክርስቲያናችንን ክብርና መዋቅራዊ አሠራር በሚፈታተኑ ግለስብእ የሚፈጸመውን ሕገ ወጥ ሥራ በማውገንዝ የኦርቶዶክስ እምነት ተከታይ የሁኑ የንዱሃን ምእመናንና ምእመናት አንድነት፤ሰላምና ፍቅር እንዲጠበቅ አስፈላጊውን ሁሉ በማድረግ ድርሻችሁን እንድትወጡና እንዲሁም ግለሰቡ ከሀገረ ስብከቱ ሊቀ ጳጳስ ፈቃድ እና እውቅና ውጪ በሰሜን አሜሪካ የሚያደርጉትን ሕገ ወጥ እንቅስቃሴ በተመለከተ በሰሜን አሜሪካ ያሉ ኦርቶዶክሳዊያን ና ኦርቶዶክሳውያት ልጆቻችን እንዳይከተሉና እንዲቃወሙ ታደርጉ ዘንድ በአክብሮት እናሳስባለን፡፡

ከመንፈሳዊ የአክብሮት ሰላምታ ጋር!

አባ ቴዎፍሎስ
የሰሜን ካልፎርንያ፣ነቫዳና አሪዞና
ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ (ዶ/ር)
Abba Theophilus (PsyD)
Archbishop of the Diocese of
Northern California, Nevada & Arizona

ግልባጭ፤

- ለኢት/ኦ/ተ/ቤ/ክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ ጽ/ቤት
- ለመንበረ ፓትርያርክ የብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርክ ልዩ ጽ/ቤት
- ለኢት/ኦ/ተ/ቤ/ክርስቲያን መንበረ ፓትርያርክ ጠቅላይ ቤተ ክህነት
- ለኢፌዲሪ ኤምባሲ ጽ/ቤት ዋሺንግተን ዲሲ
- ለኢት/ኦ/ተ/ቤ/ክርስቲያን የሰሜን አሜሪካ አህጉረ ስብከት ማዕከል ጽ/ቤት